


# Family Day Care አገልግሎቶችን የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች

AMHARIC

Australian Government
Department of Education and Training

since 1976
NSW FAMILY DAY CARE ASSOCIATION INC.

FAMILY DAY CARE መሳሪያ:

# Family Day Care አገልግሎቶችን የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች

Family Day Care አስተማሪ ለመሆን አስበው ከሆነ ወይም እንዲሆኑ ተጠይቀው ከሆነ ፍቃድ ከተሰጠው Family Day Care አገልግሎት ዘንድ መመዝገብ አለብዎ።

Family Day Care አስተማሪዎች የቅድመ ልጅነት ትምህርት በቤታቸው ለመስጠት እና አብዛኛውን ጊዜ ትንንሽ ልጆችን ለመንከባከብ ፍቃድ የተሰጣቸው ሰዎች ናቸው።

Family Day Care አገልግሎት አስተማሪዎችን እንደ ተቀጣሪዎች ወይም እንደ ትንሽ ቢዝነስ ኮንትራክተሮች በማሳተፍ የሚሰጡት አገልግሎት አካል እንዲሆኑ ያግዛሉ። አገልግሎቱ በብሄራዊ ህግ እና በቤተሰብ አገዛ ህግ መሰረት ለልጆች አገዛ ፍቃድ የተሰጠው ነው፣ ሆኖም ልጆቹን የሚቆጣጠሩት አስተማሪዎች ናቸው።

የትኛው Family Day Care አገልግሎት እንደሚመዘገቡ መምረጥ ዋነኛ ውሳኔ ነው - የሚያምኑት እና የሚፈልጉትን እርዳታ የሚሰጥዎት አገልግሎት ሰጪ ጋር መመዝገብዎን ማረጋገጥ አለብዎ።

## የ Family Day Care አገልግሎቶችየሚሰሩት ምንድነው?

- እርስዎ ልጆችን ለማስተማር እና ለመንከባከብ ትክክለኛው ሰው መሆንዎን ያረጋግጣሉ።
- ቤትዎ ልጆችን ለመንከባከብ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ይገመግማሉ።።።
- እርስዎ እንደአስተማሪ ስራዎ እንዲቀል እና ህጉ የሚጠብቅብዎትን እየሰሩ መሆንዎን ለማረጋገጥ ሊከተሏቸው የሚችሉ ፖሊሲዎች እና አሰራሮች አሏቸው።
- እንደ አስተማሪ የሚያስፈልጉዎት እንደ ኢንሹራንስ፣ ብቃቶች እና ሰርቲፊኬቶች የመሳሰሉት እንዳለዎት ።ለማረጋገጥ ማጣሪያዎችን ያደርጋሉ
- እንደ አስማሪነት ስራ ሲጀምሩ የመግቢያ ስልጠና ይሰጣሉ።
- ልጆችን በተገቢው መንገድ እየተንከባከቡ መሆኑን ለማረጋገጥ በየጊዜው ጉብኝት ያደርጋሉ።
- የትምህርት ጥራትን እና ለልጆች የሚሰጡትን እንክብካቤ በዘላቂነት ለማሻሻል አገዛ ይሰጡዎታል።
- ብቁ በሆኑ የተማሪ ቤተሰቦችን ወክለው የአውስትራሊያ መንግስት የልጆች እንክብካቤ ገንዘብ ድጋፍን ያስተዳድራሉ።
- እርስዎ ለልጆች ለሚሰጡት ትምህርትና እንክብካቤ ከቤተሰቦች ክፍያ ይቀበላሉ።
- ደምዎዝዎን ይከፍላሉ፣ ወይም የኮንትራት ስራ የሚሰሩ ከሆነ በክፍያ መጠየቂያዎ መሰረት ተገቢውን ክፍያ ይከፍላሉ።
- ቀጣይነት ያለው የስራ ቦታ ማጎልበቻ (ስልጠና) ለእርስዎ ይሰጣሉ።
- ከሁሉ በላይ፣ እንደ Family Day Care አስተማሪነትዎ ብሄራዊ ህግና ደንቦችን እንዲሁም የቤተሰብ አገዛ ህጎችን እየተከተሉ መሆንዎን በማረጋገጥ ረገድ ያግዙዎታል።

## ምርጥ ከሆነ Family Day Care አገልግሎት ጋር እንዴት መመዝገብ ይችላሉ?

ከበርካታ Family Day Care አገልግሎት ሰጪዎች ውስጥ መርጠው መመዝገብ ስለሚችሉ፣ የሚመርጡት አገልግሎት ላይ ደስተኛ መሆንዎን ማረጋገጥ አለብዎ።

ለእርስዎ ምርጥ የሆነውን አገልግሎት ለመምረጥ እንዲያግዝዎ፣ እያንዳንዱ አገልግሎት ዘንድ ስልክ ይደውሉ ወይም በአካል ይጎብኙ። እንደ Family Day Care አስተማሪነትዎ እንደት ሊረዱዎት እንደሚችሉ እና ከእርስዎ ምን እንደሚጠብቁ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። አገልግሎቱ ዘንድ ከተመዘገቡ ሌሎች አስተማሪዎች ጋር ያውሩ። አገልግሎቱ ጥሩ የሆነ ስም አለው? የአገልግሎቱ ጥራት ደረጃ ምን ያህል ነው? (ይጠይቋቸው ወይም በዚህ ድረገጽ ማየት ይችላሉ www.startingblocks.gov.au/find-child-care)

## Family Day Care አገልግሎቶችን ምን አይነት ጥያቄ መጠየቅ ይችላሉ?

የትኛው Family Day Care አገልግሎት ዘንድ መመዝገብ እንዳለብዎት ለመወሰን የሚያግዙዎት ጥያቄዎች፡

- የአገልግሎቱ **ተቀጣሪ** ነው ወይስ **ሰብ ኮንትራክተር** ነው የሚሆኑት?
- አስተማሪዎችንና ቤተሰቦችን ምን ዓይነት ክፍያዎችን ያስከፍላሉ?
- ምን ያህል አስተማሪዎች ከእነርሱ ጋር ተመዝግበዋል እንዲሁም ምን ያህል አስተባባሪዎች ቀጥረዋል? (አስተባባሪዎችእርስዎ አስማሪ ሆነው ሲሰሩ እርስዎን የሚያግዙ የአገልግሎቱ ሠራተኞች ናቸው።)
- ብቃት እንዲያገኙ ያግዙዎታል?
- የአስማሪዎች የመልቀቅ መጠን ምን ያህል ነው? (አስተማሪዎች ከረጅም ጊዜ የሚቆዩ ከሆነ በ Family Day Care አገልግሎት ደስተኛ መሆናቸውን የሚያሳይ ምልክት ነው።)
- ለአስተማሪዎች ምን ምን የስራ እድገት አገዛ ይሰጣሉ?
- በየምን ያህል ጊዜ ወደ እርስዎ ጉብኝት ያደርጋሉ?
- እርስዎ የሚንከባከቡዋቸውን ህጻናት ከሌሎች ህጻናት ጋር በቡድን ማጫወት የመሳሰሉ ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅሞችን ይሰጣሉ?



## ህጉን መከተላቸውን ያረጋግጡ!

የFamily Day Care አስተማሪ እንዲሆኑ እና በአገልግሎቱ ውስጥ እንዲመዘገቡ የጋበዘዎ ሰው አለ? የሚስማሙት በምን እንደሆነ መረዳት ያስፈልግዎታል። የFamily Day Care አገልግሎቱ ህግን የሚጥስ ከሆነ ወይም ማጭበርበር የሚፈጽም ከሆነ እርስዎም ከአስተማሪዎች እንደ አንዱ ሃላፊነት ሊወስዱ ይችላሉ። ማንኛውም Family Day Care ውስጥ የሚመዘገቡ ከሆነ እውነተኛ እንደሆነ፣ ብሄራዊ ህግን እንደሚያጥስ እና የቤተሰብ ድገፍ አገልግሎትን የሚያከብር መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ።

### ጠቃሚ ነጥቦች

- የራስዎን የFamily Day Care ቢዝነስ ሲጀምሩ ፈቃድ ካለው የFamily Day Care አገልግሎት ሰጪ ዘንድ ሊመዘገቡ ያስፈልጋል።
- የFamily Day Care አስተማሪዎች በ Family Day Care አገልግሎት መሪነት ስር ናቸው።
- አንዳንድ ጊዜ አስተማሪዎች በራሳቸው የሚሰሩ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የአገልግሎቱ ተቀጣሪዎች ናቸው።
- የFamily Day Care ቢዝነስዎን በሚመሰርቱበት ጊዜ ከየትኛው የ Family Day Care አገልግሎት ዘንድ እንደሚመዘገቡ መወሰን ዋነኛው ውሳኔ ነው። በሚመርጡት አገልግሎት ደስተኛ እንዲሆኑ ለማረጋገጥ ብዙ ጥያቄዎችን መጠየቅ አስፈላጊ ነው።
- የFamily Day Care አገልግሎቶች እነርሱ ዘንድ ለተመዘገቡ አስተማሪዎችየተለያዩ ድጋፎችን የመስጠት ግዴታ አለባቸው። ይህም የመግቢያ ስልጠናን፣ ቀጣይነት ያለው የሙያማጎልበቻ እና ተከታታይ ድጋፍን የሚያካትት ነው።
- አንዳንድ የFamily Day Care አገልግሎቶች ዝቅተኛ የሆነ የአስተዳደር ክፍያዎችን ሊያቀርቡ ይችላሉነገር ግን የሚያስፈልግዎትን አገልግሎት ላይሰጡዎ ይችላሉ። ዝቅተኛ ዋጋ ስላላቸው ብቻ አይመዝገቡ።
- ብሄራዊ ህግን እና የቤተሰብ ድጋፍ ህግን ይጥሳል ብለው የሚጠረጥሩት Family Day Care አገልግሎት ዘንድ አይመዝገቡ። ይህ ህግን በመጣስ ስጋት ውስጥ ሊጥልዎ ይችላል።
- እንደ Family Day Care አስተማሪነትዎ በስራዎ ውስጥ ድጋፍ እንደሚያገኙ የሚያረጋግጥልዎ ምርጥ መንገድ ድጋፍ የሚያደርግልዎ እና የሚያምኑት Family Day Care አገልግሎት ዘንድ መመዝገብ ነው።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### በFamily Day Care አገልግሎት ውስጥ ልመዘገብ ያስፈልጋል?

አዎን። የFamily Day Care አስተማሪ ለመሆን ፈቃድ ባለው የFamily Day Care አገልግሎት ዘንድ ሊመዘገቡ ያስፈልጋል።

### የተለያዩ የFamily Day Care አገልግሎት ዓይነቶች አሉ?

አዎን። አንዳንዶች ለትርፍ ያልተቋቋሙ ናቸው።

### የትኛው አገልግሎት ዘንድ መመዝብ እንደምችል እንዴት መወሰን እችላለሁ?

እነዚህን ነገሮች ከግንዛቤ ያስገቡ፡-

- ምን አይነት ድጋፍ ይሰጡዎታል።
- ሲጀምሩ ምን ዓይነት ስልጠና ይሰጡዎታል።
- አስተማሪዎችንና ወላጆችን የሚያስከፍሉት ክፍያ ምን ያህል ነው።
- ምን አይነት የሙያ ማጎልበቻ/ ስልጠና ይሰጣሉ።
- በየምን ያህል ጊዜ ይጎበኙዎታል።
- የአገልግሎት ጥራት ደረጃው ምን ያህል እንደሆኑ (ይህንን ከዚህ ድረ-ገጽ ማወቅ ይችላሉ www.startingblocks.gov.au/find-child-care)
- ከመንግስት ተቀብለው ብቁ የሆኑ ቤተሰቦችን በመወከል የሚያስተዳድሩትን የልጆች እንክብካቤ የድጋፍ ገንዘብ በተመለከተ ብሄራዊ ህግ እና ደንቦችን እንዲሁም የቤተሰብ እገዛ ህግን ምን ያህል በተገቢው ሁኔታ ይከተላሉ።

### ድርጊትን ማሳወቅ

የማጭበርበር ድርጊት አለ ብለው የሚያስቡ ከሆነ ከአውስትራሊያ መንግስት የትምህርትና የስልጠና ዲፓርትመንት ድርጊት ማሳወቂያ ከበቂ ዝርዝር ጋር በ 1800 664 231 ይደውሉ ወይም በ tipoffline@education.gov.au ኢሜል ይድርጉ። ከፈለጉ ማንነትዎን አለማሳወቅ ይችላሉ።




## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች
## የቀጠለ

### ተጨማሪ አገልግቶችን የት ማግኘት እችላለሁ?

በአቅራቢያዎ ያሉ አገልግሎትን ለማግኘት፣ www.fdca.com.au ይግቡና ‘find childcare’ የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።

### ምን ምን ጉዳዮች ሊያሳስቡኝ ይገባል?

አገልግሎቱ ብሄራዊ ህግን ወይም ቤተሰብ ድጋፍ ህግን እንደሚተላለፍ የሚያስቡ ከሆነ ሊያሳስብዎ ይገባል።

የሚሰጡት አገልግሎት እውት ለመሆን በጣም የተጋነነ ከሆነ ሊያሳስብዎ ይገባል።

### Family Day Care ን የሚያቅፉ ህጎችን እና ደንቦች ምን ምን ናቸው?

Family Day Care አገልግሎቶች እና አስማሪዎች እንዴት መስራት እንዳለባቸው የሚቆጣጠሩ ብዙ ህጎች አሉ።

ዋና ዋናዎቹ ህጎች እነዚህ ናቸው፡

- የትምህርት እና እንክብካቤ አገልግሎቶች ብሄራዊ ህግ
  www.acecqa.gov.au/national-law
- የትምህርት እና እንክብካቤ አገልግሎቶች ብሄራዊ ደንብ
  www.acecqa.gov.au/national-regulations
- የቤተሰብ የድጋፍ ህግ፡
  www.education.gov.au/family-assistance-law-0

### የበለጠ ይወቁ

ፍላጎት አለዎት? የበለጠ ለማወቅ ወደ እነዚህ ድረገጾች ይሂዱ፡

- **www.education.gov.au/compliance**
- **www.fdcsupport.org.au**
- **www.fdca.com.au**
- **www.acecqa.gov.au**

ወይም በአቅራቢያዎ ወዳሉ Family Day Care አገልግሎቶች ይሂዱ።
(በአቅራቢያዎ ያሉ አገልግቶችን ለማግኘት፣ **www.fdca.com.au** ይሂዱና ‘find childcare’ የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።)

Australian Government
Department of Education and Training

NSW FAMILY DAY CARE ASSOCIATION INC.